# መዘክር

## ወሬ ለምዶ

ከልጅነት ጨዋታ ማጋጣነት
በስንፍና ማመንታት ዋልጌነት፣
ልቦናው ሁሌም ሲያመነታ
ዛሬ ነገ እያለ ሳይበረታ።

ጊዜ ለማሳለፍ በወሬ ፈዛዛ
ወሬ በወሬ ተገንብቶ ሲጠነዛ፣
ፋይዳም ላይሞላ የወሬ ልምድ
ምንም ላይጠቅም ነገር ሲገምድ።

ሲያወራ የባጥ ቆጡን ሲቀባጥር
እንዲያ ሲል አድኀበት ሳይጠረጥር፣
ለውጥ አያመጣ እንደሁ ሁሉም ከብዶ
በሥራ ሳያተኩር ወሬ ለምዶ።

የወሬም ወሬ ሲነታተብ
የውሸት ብዛት ሲያስከታትብ፣
ይሉኝታም የለሽ ኀሊናው
አዙሮ ላያስተውል እንዳይወቅሰው።

ቢባል ቢባል ቢደከም ላይማር
ውጤት ለማምጣት መልካም ተግባር፣
ሳይቻል ሲቀር ያሳዝናል
ጊዜውም በከንቱ እንዲያው ያልፋል።

ዛሬም በሥራ ሳያተኩር ወሬ ለምዶ
በዝባዝንኬ ድርጊቶቹ ተጠምዶ፣
ሲደነግጥ ሲባንን ያልፈጸመው ትዝ ሲለው
በሰመመን ብቻ የተሳካ ሲመስለው።

የብዙ ወገን ጥፋቱን
ምነው ቢረዳ ከንቱነቱን፣
የወሬ ልማድ ክፋቱን
ሥራ መተግበር ጥሩነቱን።

በግሉ ብቻ ታውሮ
የሰው ላይሰማ ደንቁሮ፣
መሻሻል ሳያመጣ ሲዳክር
በወሬ ዘመኑን ሲቆጥር።

እድገት ለማትረፍ ሲጣጣሩ
ብዙ በማቀድ ሲሞክሩ፣
ሌሎች መሻሻል ያሳያሉ
ብርታት ለሥራ ይለፋሉ
ተገቢውን ውጤት ያተርፋሉ።

ለከንቱ ወሬ ቦታ መገኘቱ
የሞራል ብቃት መታጣቱ፣
ዕውነቱን መፈለጉ ሲጠፋ
የሃሰትና ክህደት ወሬ ሲስፋፋ።

ምናለ አጉል ባሕል ባይወለድ
በወሬ ሕልም ባይታቀድ፣
ባይቀየስ ትውልዱ መመሪያው
ጥሩ ምግባር ቢሆን መለኪያው።

ዓለማየሁ አስፋው / ቶሮንቶ